የሰበር መ/ቁ 252364

ታህሳስ 26 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

በእውቀቱ በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

አመልካች፡- 1. ዶ/ር አምሀ አቻምየለው ይግዛው

2. ዶ/ር ዘካሪያስ ታዬ ሲሳይ

3. ሲ/ር አይናዲስ ሀብታሙ

ተጠሪ፡- የአዲስ አበባ የምግብ፤የመድሃኒትና የጤና እንክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍርድ**

መዝገቡ ለዚህ ችሎት የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ301299 በቀን 26/10/2015 ዓ.ም በሰጠው ብይን እንዲሁም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት መ/ቁ/250663 በቀን 25/11/2015 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ስልጣኑ አይቶ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑን ጠቅሶ ጉዳዩን በይግባኝ አይቶ ለመወሰን የስረ ነገር ስልጣን የለውም ብሎ በመወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሟል በሰበር እንዲታረምልን ሲሉ አመልካቾች አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ሲታይ አመልካቾች በግንቦት 28 ቀን 2015 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ በተጠሪ በኩል የተወሰደባቸው አስተዳደራዊ እርምጃ ማለትም 1ኛ አመልካች ከቀዶ ህክምና በኃላ አካላዊ ምርመራ ባለማድረግና ባለመፃፍ፤ባለማስተላለፍ፤ታካሚዋ አስጊ ሁኔታ ላይ መሆናቸው ሲገለፅላቸው እርምጃ ባለመውሰዳቸውና በቦታው ባለመገኘታቸው በሚል የጤና ሙያ ፈቃዳቸው ለ1 ዓመት እንዲታገድ፤2ኛ አመልካች የበላይ ሀኪም በመጥራት ክትትል እንዲደረግ ባለማድረጋቸውና በቂ ክትትል ባለማድረጋቸው ለ6

ወራት የሙያ ፈቃዳቸው እንዲታገድ እንዲሁም 3ኛ አመልካች ከቀዶ ህክምናው በኃላ የነበረው ክትትል የተሟላ ባለመሆኑና የታካሚዋ ጤና ሳይወሳሰብ በፊት ለበሳል ጤና ባለሙያዎች ባለማስተላለፋቸው በሚል የሙያ ፈቃዳቸው ለ9 ወራት እንዲታገድ የአ.አ የጤና ባለሙያዎች ስነ-ምግባር ኮሚቴ በመመሪያ ቁጥር 1/2007 አንቀፅ 35(8) እና 33(1)(ረ) መሰረት በቁጥር የጤ/ባ/መ/ቁ/164/2013 የውሳኔ ሀሳብ ቀርቦ የተጠሪ መስሪያ ቤት ዋና ዳይሬክተር የውሳኔ ሀሳቡን በግንቦት 02/2015 በማፅደቅ የአመልካቾች የሙያ ፈቃድ እንዲታገድ በማድረጉ አመልካቾችም ይህ ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሰረት ሊከለስ ይገባል ሲሉ አቤቱታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ተጠሪ ማስረጃ በሚገባ ሳያደምጥና ሳይመረምር ወስኗል፤አመልካች በግዴለሽነት ጉዳት አድርሰዋል በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ተገቢ አይደለም፤ አመልካቾች የታካሚዋን የጤና ሁኔታ ለማሻሻል ከፍተኛ ሙያዊ ጥረት አድርገናል፤በአዲስ አበባ የጤና ባለሙያ ስነ-ምግባር ኮሚቴ መመሪያ ቁጥር 01/2007 አንቀፅ 33(7) መሰረት አንድን ጥፋት ከባድ የሚያስብለው የተፈፀመው የሙያ ስነ-ምግባር ከፍተኛ የጤና ችግር የሚያስከትል ሲሆን ነው፤በተያዘው ጉዳይ ታካሚ የሞተች በመሆኗ ይሄ ተፈፃሚነት የለውም፤ታካሚዋ የሞተች ቢሆንም የሞቷ ምክንያት በአስክሬን ምርመራ አልተረጋገጠም፤ 1ኛ አመልካች ለታካሚዋ ሞት ምክንያት ስለመሆናቸውም ኮሜቴው አላረጋገጠም፤ በወንጀልም አልተጠየቁም፤ ያቀረብናቸው የሰነድ ማስረጃዎች ሙያዊ ጥፋት መፈፀማችንን አያሳዩም፤የተሰጠው ውሳኔም ለባለስልጣኑ በመመሪያው ከተሰጠው ስልጣን ውጭ ነው፤የተሰጠው እግድም ተፈፀመ ተብሎ ኮሜቴው ከደረሰበት ድምዳሜ ጋር የማይመጣጠን ባለመሆኑ አስተዳደራዊ ውሳኔው ሊከለስ ይገባል ሲሉ አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ አመልካቾች አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ የአ/አ ከተማ አስተዳደር የጤና ሙያ ስነምግባር ኮሜቴ መመሪያ ቁጥር 120/2014 መሰረት ያደረገ ነው፤በመመሪያውም መሰረት በተሰጠው አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅሬታ ያለው ሰው ጉዳዩን በይግባኝ ወደሚመለከተው ፍ/ቤት አቅርቦ የማስወሰን መብት እንዳለው ተደንግጓል፤ የአመልካቾች አቤቱታ በጥቅልም ሆነ በዝርዝር ሲታዩ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሰረት አስተዳደራዊ ውሳኔ ክለሳ የሚጠይቁ አይደሉም፡ይልቁኑም በይግባኝ ቀርበው ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው፡፡ይህንኑም በይግባኝ ደረጃ መርምሮ ውሳኔ እንዲሰጥ በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል በአስተዳደሩ ስር የተቋቋመው የአ/አ/ ከተማ ፍ/ቤት ለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀፅ 43 (3) ስር ተመላክቶ ይገኛል፡፡በመሆኑም የአመልካቾች አቤቱታ አስቀድሞ በህግ ለፍ/ቤቱ የተሰጠ ጉዳይ ነዉ በሚል አመልካች ያቀረቡት የዳኝነት ጥያቄ በአዋጅ 1183/2012 መሰረት ለችሎቱ የሚቀርብ የክርክር ጉዳይ ሆኖ ባለመገኘቱ ችሎቱ በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ/231(1) መሰረት ጉዳዩን ተቀብሎ ውሳኔ ለመስጠት ስልጣን የለውም ሲል ብይን ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች በውሳኔው ላይ ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ችሎቱ የይግባኝ አቤቱታውን ተመልክቶ በአዋጅ ቁጥር 1183/2012 በአስተዳደራዊ ውሳኔ ላይ የዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይግባኝ ስልጣኑ አይቶ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑን የአዋጁ አንቀፅ 49(1) ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት የቀረበውን ይግባኝ አይቶ ለመወሰን የስረ ነገር ስልጣን የለውም ሲል በአብላጫ ድምፅ ወስኗል፡፡አቤቱታዉ ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበዉ በዚህ ላይ ነዉ፡፡

የአመልካቾች ነሃሴ 15/2015 ዓ.ም ጽፎ ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭር፡- የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካቾች ጉዳይ በአዲስ አበባ የጤና ባለሙያዎች ስነ-ምግባር ኮሚቴ መመሪያ ቁጥር 120/2014 መሰረት ቅሬታ ያለው ሰው አግባብ ላለው ፍ/ቤት ይግባኝ የማለት መብት አለዉ፤የአመልካቾችም ጥያቄ በይግባኝ ደረጃ የሚታይ እንጂ በፌዴራል የአስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጁ ቁጥር 1183/2014 መሰረት ቀርቦ የሚታይ አይደለም ሲል መወሰኑ ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 200289 በቀን ጥቅምት 25/2014 ዓ.ም ከህክምና አገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን አይቶ ለመወሰን ስልጣን ያላቸው የአ/አ ከተማ ፍርድ ቤቶች ሳይሆኑ የፌዴራል የአስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሰረት ነው በማለት የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሚቃረን ብይን በመሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል፤ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለኝም በማለት ብቻ የሰጠውን ብይን ጠቅላይ ፍርድ ቤት እንደመጨረሻ ውሳኔ መቁጠሩ አግባብነት የሌለው እና የፌዴራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 2(4)(ለ) መሰረት ያላደረገ ነው፡በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ301299 በቀን ሰኔ 26/2015 ዓ.ም የሰጠው ብይን ተሽሮ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን የማየት የስረ- ነገር ስልጣን አለው እንዲባል፤የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይ/መ/ቁ 250663 በቀን 25/2015 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ህግን ያለአግባብ በመተርጎም በመሆኑ በይግባኝ ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው እንዲባል ሲሉ አመልክተዋል፡፡

ሰበር አጣሪ ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካቾች የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ ላይ እና የተጠሪ የመወሰን ስልጣን ላይ ያቀረቡት የዳኝነት ክለሳ በፌዴራል የአስተዳደር ስነ-ስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 መሰረት በከፍተኛ ፍ/ቤት የሚታይ አይደለም መባሉ በህግ ከተሰጠው ስልጣን እና ሰበር ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 200289 ከሰጠው ትርጉም አንፃር ህጋዊ ስለመሆኑ፤የስር ከፍተኛ ፍርድ ቤት አስተዳደራዊ ውሳኔውን እንዲከለስ የሰጠው ውሳኔ ሳይኖር ውሳኔው የመጨረሻ ነው በሚል ይግባኙን አለመቀበሉ ዜጎች በህገ-መንግስቱ ካላቸው ፍትህ የማግኘት መብትና በስነ-ስርዓት ህጉ ከተዘረጋው የይግባኝ መብት ስርዓት አንፃር ውሳኔው

መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት መሆን አለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪ መልስ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በቀን 07/01/2016 ዓ.ም የተጻፈ መልስ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም ባጭሩ፤ውሳኔውን ያስተላለፈው የአዲስ አበባ የጤና ባለሙያዎች የስነ-ምግባር ኮሚቴ መመሪያ ቁጥር 120/2014 አንቀፅ 37 ንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ድንጋጌዎች መሰረት ይግባኝ መጠየቅን በሚመለከት በኮሚቴው በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የህግ ወይም የስነ-ሥርዓት ጥሰት ተፈፅሟል ብሎ የሚያምን አካል ውሳኔው በተላለፈ በ30 ቀናት ውስጥ አግባብነት ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ስለመቻሉ ተደንግጓል፤ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀፅ 43/3 ላይ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ለአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በልዩ ሁኔታ ሰጥቶ ባለበት የአስተዳደር ውሳኔዎች ክለሳ ሙሉ ለሙሉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ መድረስ አግባብነት የለውም፤በአስተዳደራዊ ውሳኔዎች ላይም የአስተዳደር ስነ ስርዓት አዋጁን በሰፊው ወይም በተለጠጠ መልኩ ገቢራዊ ማድረግ በፌዴራልና በአዲስ አበባ ከተማ ፍ/ቤቶች፤በአስተዳደር ፍርድ ቤትና በሌሎች በህግ የመዳኘት ስልጣን በተሰጣቸው አካላት የሚታዩ ክርክሮችን ሙሉ በሙሉ በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክለሳ የሚታዩ ናቸው ወደሚል ድምዳሜ የሚወስድና እነዚህን የዳኝነት አካላት ሚና የሚያሳጣና በከፍተኛ ፍ/ቤቱም የስራ ላይ ጫና የሚፈጥር በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ብይን ሊነቀፍ የማይገባ በመሆኑ የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ ይደረግ በማለት ተከራክሯል፡፡አመልካቾች የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም ያስቀርባል ሲባል የተያዘውን ጭብጥ መሰረት በማድረግ ከግራቀኙ ክርክር፤ከስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ እና ከተገቢው የህግ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ የአመልካቾች አቤቱታ መነሻዉ በተጠሪ ተቋም የስነምግባር ኮሚቴ ታይቶ የቀረበዉን ዉሳኔ ሃሳብ የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር በማጽደቁ ይህ አስተዳዳራዊ ዉሳኔ ስህተት አለበት የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር በአዋጅ ቁጥር 1183/2013 መሰረት በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲከለስ በሚል ማመልከታቸዉን መዝገቡ ያሣያል፡፡ይሁንና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በስረነገር ጉዳይ ሳይገቡ የዳኝነት ስልጣን የለንም በማለት መዝገቡን ዘግተዋል፡፡አመልካቾች አጥብቀዉ የሚቃወሙት ሁለቱም የስር ፍርድ ቤቶች ጉዳዩን በአግባቡ ሳይመረምሩ የዳኝነት ስልጣን የለንም ማለታቸዉ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ፤ፍትህ የማግኘት ህገ መንግስታዊ መብት ጋር ይጣረሳል በማለት ነዉ፡፡

በመሰረቱ ማንኛዉም ሰዉ በፍርድ ሊወሰን የሚገባዉን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠዉ አካል የማቅረብና ዉሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለዉ የኢፌዲሪ ህግ መንግስት አንቀጽ 37(1) ላይ ተደንግጓል፡፡በተያዘዉ ጉዳይ ተጠሪ ተቋም በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለዉ ወገን አቤቱታ ሊያቀርብበት የሚችል መሆኑ አላከራከረም፡፡አከራካሪዉ ነጥብ ተጠሪ ተቋም በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ የሚቀርብ አቤቱታ ለማየት ስልጣን ያለዉ አካል ማነዉ? የሚለዉ ነዉ፡፡በመሰረቱ በፍርድ ቤት ወይም ከፊል የዳኝነት ስልጣን በተሰጠ አካል በተሰጠ ዉሳኔ ላይ ይግባኝ ማቅረብ መብት ሲሆን ይግባኙን ለማየት ስልጣን ያለዉ አካል የሚለየዉ በህግ የተዘረጋዉን ስርዓት ተከትሎ ነዉ፡፡በመሆኑም በቀዳሚነት መመርመር ያለበት ጉዳይ ቅሬታ የቀረበበት ዉሳኔ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ነዉ ወይስ አይደለም የሚለዉ ነዉ፡፡ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት የፌደራል አስተዳደር ስነስርዓት አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ላይ የተሰጠዉን ትርጉም ማየት ተገቢ ነዉ፡፡በዚህ አዋጅ ትርጉም ክፍል ላይ እንደተመለከተዉ "የአስተዳደር ዉሳኔ" ማለት መመሪያ ማዉጣት ሳይጨምር የአስተዳደር ተቋም በእለት ተእለት ተግባሩ በሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ የሚሰጠዉ የአስተዳደር ዉሳኔ ነዉ፡፡የአዋጁን አንቀጽ 2(2) ይመኪቷል፡፡ አስተዳደር ተቋማት በህግ በተሰጣቸዉ የስልጣንና ሃላፊነት መሰረት የሰዎች መብት ወይም ጥቅም የሚመለከት ጉዳይ ዉሳኔ የሚሰጡት በተቋሙ አነሳሽነት ወይም ጉዳዩ በሚመለከተዉ ሰዉ አመልካችነት ሊሆን ይችላል፡፡ተቋማቱ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ሲሰጡ የሚመሩባቸዉ መርሆዎችም እና የሚከተሉዋቸዉ ስነስርዓት በአዋጁ ክፍል ሶስት ላይ በዝርዝር ተደንግጓል፡፡ከአዋጁ መግቢያም ሆነ ከድንጋጌዎቹ ዝርዝር ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለዉ አዋጁ ያስፈለገበትን ምክንያት የአስተዳደር ተቋማት የውሳኔ አሰጣጥና የመመሪያ አወጣጥ የሚመራባቸዉን መርሆዎችንና ስነስርዓት መዘርጋት ሲሆን በሌላ በኩል በአስተዳደራዊ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ቅር የተሰኘ ሰው የውሳኔዎቹንና የመመሪያዎቹን ህጋዊነት በፍ/ቤት የሚያስመረምርበትን ስርዓት በመደንገግ አስተዳራዊ ፍትህ ለማስፈን ነዉ፡፡በጥቅሉ ሲታይ ይግባኝም ሆነ ክለሳ ስርዓት የተዘረጋበት ዋነኛ ዓላማ ስህተት ያለበት ዉሳኔ የሚታረምበት እድል ለመፍጠር ሲሆን አቤቱታ(ቅሬታ) አቀራረብ ስነስርዓትም ሆነ ይዘት ላይ ግን በሁለቱ መካከል መሰረታዊ ልዩነት መኖሩን ነዉ፡፡በዚህ ረገድ የክለሳ ስነ ስርዓት ትኩረት የሚያደርገዉ በዉጤቱ ላይ ሳይሆን በሂደቱ እና በምክንያታዊነቱ ላይ ሲሆን ይግባኝ ስነ ስርዓት ግን በሂደቱም ሆነ በዉጤቱ ላይ ያለዉን ጉድለት ለማረም ሰፋ ያለ እድል የሚሰጥ መሆኑ ይታወቃል፡፡ስዚህም የክለሳ ስርዓት በጠባቡ የሚተገበር ከመሆኑ አኳያ የይግባኝ ስርዓት በተለያየ የህግ ስርዓት ተመራጭ ሆኖ ይወሰዳል፡፡እንደሚታወቀዉ የመንግስት አስተዳደር (የመንግስት አስፈጻሚ አካል) አካላት ህግ ከማስፈጸም ባሻገር በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ህግ የማዉጣት እና ከፊል የዳኝነት ስልጣን መስጠት የተለመደ ጉዳይ ነዉ፡፡ይሁንና እነዚህን ተግባራት ሲያከናዉኑ በህግ በተሰጣቸዉ ስልጣን ወሰን መሰረት መሆን አለመሆኑን እንደአግባብነቱ በህግ አዉጪዉ እና/ወይም በዳኝነት አካል ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት ስርዓት መዘርጋትና

ተግባራዊ ማድረግም የተለመደ አሰራር ነዉ፡፡አስተዳደራዊ ዉሳኔ በዳኝነት አካል እንዲከለስ የሚደረገዉም የዉሳኔዉን ህጋዊነት ለማረጋገጥ እንደሆነ እሙን ነዉ፡፡

በተያዘዉም ጉዳይ በተጠሪ ተቋም የተሰጠዉ ዉሳኔ በይግባኝ ለማየት ስልጣን ያለዉ የአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች (አዋጅ ቁጥር 361/95 ይመለከታል) ወይስ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነዉ (አዋጅ ቁጥር 1183/2012 ይመለከታል) የሚለዉ ለመለየት ዉሳኔዉን ይዘትና ዉሳኔ የተሰጠበትን አግባብ መመርመር ይገባል፡፡ከዚህ አኳያ ሲታይ ለአቤቱታ መነሻ ሆነዉ ዉሳኔ የተሰጠዉ በከተማዉ አስተዳደር የምግብ፣የመድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን በወጣዉ የጤና ሙያ ስነምግባር ኮሚቴ መመሪያ ( መመሪያ ቁጥር1/2007 ተብሎ የተጠቀሰ ሲሆን በፍትህ ሚ/ር ሲመዘገብ መመሪያ ቁጥር 120/2014 ተብሎ መመዝገቡ ተጠቅሷል ) መሰረት የግራቀኙ ክርክርና ማስረጃ ተሰምቶ ስለመሆኑ መዝገቡ ያሣያል፡፡በዚህ መመሪያ አንቀጽ 37(2) ስር እንደተመለከተዉ በዉሳኔዉ ላይ የህግ ወይም የስነስርዓት ጥሰት ተፈጽሟል የሚል ወገን ዉሳኔዉ በተላለፈ በ30 ቀን ዉስጥ ይግባኙን አግባብነት ላለዉ ፍርድ ቤት ማቅረብ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡አግባብነት ያለዉ ፍርድ ቤት ማነዉ? የሚለዉ ግልጽ ስላልነበር በተመሳሳይ ክርክር ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ 145733 ላይ በሰጠዉ ገዥ ዉሳኔ እንዳመላከተዉ የከተማዉ አስፈጻሚ አላካት ዉሳኔ ጋር በተያያዘ ስልጣን ያለዉ አካል የከተማዉ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት መሆኑን ዉሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ይሁንና ከዚህ ሰበር ችሎት ዉሳኔ በኋላ የፌዴራል አስተዳደር ስነስርዓት አዋጅ መዉጣቱን ተከትሎ የአ/አ/ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሪን ጨምሮ የፌዴራል መንግስት አስፈጻሚ አካላት የሚሰጥ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ላይ የክለሳ ጥያቄ አቤቱታ የሚቀርበዉ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት መሆኑን አዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ49 መሰረት በማድረግ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/200289 ላይ ገዥ ዉሳኔ መስጠቱን ልብ ይለዋል፡፡ይህ አቤቱታ ለዚህ ሰበር ችሎት የቀረበዉ የስር ፍርድ ቤቶችን ዉሳኔ አግባብነት ከዚህ የሰበር ችሎቱ ዉሳኔ አኳያ ለመመርመር ነዉ፡፡እኛም መርምረን እንደተገነዘብነዉ ሰበር መ/ቁ/ 200289 ላይ ለዉሳኔ መሰረት የሆነዉ አቤቱታ ያቀረበዉ ዮርዳኖስ የአጥንት የህክምና ማእከል በተደጋጋሚ ተመሳሳይ የህክምና ስህተት ፈጽሟል በሚል ለሶስት ወር እንዲዘጋና ፈቃዱን እንዲመለስ የተሰጠ አስተዳደራዊ ዉሳኔ በመቃወም ነዉ፡፡በያዝነዉ ጉዳይ ደግሞ አመልካቾች ሙያዊ ስህተት ፈጽመዋል ተብሎ ክስ ቀርቦባቸዉ በስነምግባር ኮሚቴ ተምርምሮና ማስረጃ ተሰምቶ ዉሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ ነዉ፡፡ስነምግባር ኮሚቴ ከፊል የዳኝነት ስልጣን የተሰጠዉ አካል ነዉ ተብሎ በህግ በግልጽ የተደነገገ ባይሆንም ሙያዉ ካለዉ ልዩ ባህርይ አኳያ የህክምና ባለሙያዎች ሙያዊ ስነምግባር አክብረዉ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ እና ቅሬታ ሲቀርብ ቅሬታዉ ተምርምሮ የሚወሰንበት የስነስርዓት መመሪያ ወጥቶለት ተግባር ላይ የዋለ መሆኑ ሲታይ ክርክሩ የተመራበት ስነስርዓት የዳኝነት መሰል እንደሆነ ያሣያል፡፡ከዚህ አንጻር ሲታይ በኮሚቴዉ በተሰጠ ዳኝነት ላይ በስነስርዓትም ሆነ በዉጤት ረገድ የተፈጸመ

ስህተት መኖር አለመኖሩን ለመመርመር ስልጣን ያለዉ አካል የዳኝነት አካል ነዉ መባሉ አመልካቾችን መብት የሚያጣብብ ነዉ የሚያሰኝ ምክንያት የለም፡፡ስለዚህም ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/2002189 ላይ ዉሳኔ የሰጠበት ጉዳይ እና አሁን የቀረበዉ ጉዳይ ባህርይም ሆነ ክርክሩ የተመራበት አግባብ ልዩነት እንዳለዉ ያሣያል፡፡ይህ ከሆነ ደግሞ ሰበር ችሎቱ በመ/ቁ/200289 የሰጠዉ ዉሳኔ ለዚህ ጉዳይ ተፈጻሚ ማድረግ አግባብነት ያለዉ ሆኖ አላገኘንም፡፡

ሲጠቃለል በተጠሪ ተቋም የሙያ ስነምግባር ከሚቴ ታይቶ በተቋሙ በጸደቀዉ ዉሳኔ ላይ አመልካቾች ቅሬታቸዉን በይግባኝ ስልጣን ላለዉ ፍርድ ቤት ከሚያቀርቡ በስተቀር በአስተዳደር ስነስርዓት ህግ በክለሳ ስርዓት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚቀርብ አይደለም ተብሎ ዉድቅ መደረጉም ሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ከአዋጅ ቁጥር 1183/2012 አንቀጽ 49(1) አኳያ ይግባኝ የሚቀርብበት አይደለም በማለት በሰጠዉ ትእዛዝ ላይ በዚህ ሰበር ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ ህግ ስህተት ተፈጻመበት ነዉ የሚባልበት ምክንያት አላገኘንም፡፡በዚሁ አግባብ ተከታዩንነዉሳኔ ሰጥተናል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1ኛ/የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/301299 ላይ በቀን 26/10/2015ዓ.ም የሰተዉ ብይን እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/250663 ላይ በቀን 25/11/2015ዓ.ም የሰጠዉ ትእዛዝ በሰበር ስነስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 9(1/ሀ) መሰረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ ችሎት የተደረገዉ ክርክር ወጪና ኪሳራ ግራቀኙ የየራሳቸዉን ይቻሉ ብለናል፡፡

**መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/ተ